

# የትንቢት ቃል

ስድስተኛ ዓመት, ቁጥር2

ታሕሳስ 2004

ወቅታዊ የአድቬንቲስት መጽሔት

## «ሰው ሰራሽ ወግና ስርዓትን እያስተማረ በከንቱ ያመልከኛል»

በአንድ ወቅት የሰንበት ትምህርት ክፍለ ጊዜ ላይ «ለተለያዩ የክርስትና ዘርፎች/ቤተክርስቲያናት መፈጠር/መፈልፈል ምክንያቱ ምንድን ነው?» የሚል ጥያቄ ተነሳና ብዙዎቻችን የመሰለንን አስተያየት ሰጠን። በአብዛኛው የሌላውን የዶክትሪን ስህተት በማጉላት ውይይታችን ደራ። በመጨረሻ ግን ትክክለኛውን መልስ ያገኘነው የጥናታችን ዋቢ ከሆነው ከራሱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ነበር። ይኸውም በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 15፥8–9 ላይ የሰፈረው ቀደም ሲል ኢሳይያስ የተነበየው በኋላም ኢየሱስ ሊከሱት ለቀረቡት ፈሪሳውያንና የሙሴ ሕግ መምህራን የተናገረው «ይህ ህዝብ በአፉ ያከብረኛል ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው። ሰው ሰራሽ ወግና ስርዓትን እንደ ሕግ አድርጎ እያስተማረ በከንቱ ያመልከኛል» የሚለው ጥቅስ ነው።

ከጥንት ወላጆቻችን ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ ለመንፈሳዊ ሕይወት ውድቀታችንና ከእውነት ለመራቃችን ዋነኛው ምክንያት እራሳችንን ለቃሉ በማስገዛት እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ ከመኖር ይልቅ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ቃሉን ለኛ እንደሚስማማ በመጠምዘዝ በቃሉ ስም ፍላጎታችን ለማሳካት የምናደርገው ጥረትና እሩጫ ነው።

እግዚአብሔር በሚፈልገውና ባዘዘው መንገድ ሳይሆን እኛ በምንፈልገውና በሚመቸን መንገድ ሰው ሰራሽ ወግና ስርዓትን እንደ ሕግ አድርገን በማስተማርና በመከተል ምን ያህል እውነትን እንዳዳቀልነውና እንደበረዝነው ለመገንዘብ እንዲያመቸን የሚከተሉትን አብይ ሀሳቦች በማስረጃነት እንመልከት።

**ሰንበት**

የሰንበት ቀን ሃጥያት ወደምድር ከመግባቱ በፊት ለሰው ዘር ሁሉ የተሰጠ የጌታ የእረፍት ቀን ነው። ዘመኑም ከሰው ዘር እድሜ ጋር እኩል ነው፤የተሰጠውም ለሰው ልጆች ጥቅም ነው (ማር 2፥27)። ከሌሎቹ ስድስት ቀናት የማናገኘውን የተለየ መንፈሳዊ በረከት የምንቀበልበት ዕለት ነው (ዘፍ 2፥3)። ሰንበት የጌታን ፈጣሪነት በተለየ ሀ ነ ታ ያስታውሰናል (ዘፍ 20፥8–11)። የሰው ዘር ሁሉ እግዚአብሔርን በፈጣሪነቱ ሊያከብረውና ሊያመሰግነው ይገባል (ራዕ 14፥7)። በቅዱስ ቀኑ ከእለት ተግባራችንና ከከንቱ ወሬ በመቆጠብ (ኢሳ 58፥13) እግዚአብሔርን እንደ አምላክነቱ (ዘፍ 20፥8–11) ልናመልከው ይገባል። ያኔ በጌታ ደስ ይለናል (ኢሳ 58፥13፤14)። ሰንበት ከአስርቱ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ትዕዛዛት አንዱ ነው። ሰንበትንም ሆነ ቀሪዎቹን ዘጠኙን ትዕዛዛት ለመጠበቃችን ማረጋገጫው ለእግዚአብሔርና ለሰው ልጆች ያለን ፍቅር ነው። (ዮሐ 14፥15፤ 1ዮሐ 5፥2፤3)



ሰንበት ቅዳሜ መሆኑን ከላይ የጠቀስነው የቅዱስ ቃሉ ክፍል ያረጋግጥልናል። በአንፃሩ ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ዮሐንስ ባለው ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቢፈለግ የእሁድን ሰንበትነት የሚያረጋግጥ ቀርቶ የሚያመለክት አንድም ቃል አይገኝም። የቋንቋ ተመራማሪዎች በ140 የአለም ቋንቋዎች ቅዳሜ «ሰንበት» ተብሎ እንደሚጠራ አረጋግጠዋል።

የመጀመሪያው ታሪካዊ እሁድን እንደ እረፍት ቀን/ሰንበት የመጠበቅ አስገዳጅ ሕግ የታወጀው ማርች 7ቀን 321 ዓ.ም. በወቅቱ የአሕዛብ ንጉሥ በነበረው በቆንስጣንጢኖስ ነበር። አዋጁ ከወጣ በኋላም አራተኛውን ትዕዛዝ በመጠበቅ የእግዚአብሔርን ሰንበት ሰባተኛውን ቀን ማክበር የቀጠሉ ክርስቲያኖች የመንግሥትና የቤክርስቲያን ጠላቶች ተብለው ተፈረዱ። እንዲወገዙና እንዲረገሙም ተደረገ (መለከት መጽሔት ልዩ እትም 2002 ገጽ12)። በመቀጠልም ኢየሱስ ክርስቶስ አንድኗንም ትዕዛዝ እንዳልሻረና (ማቴ 5፥17፤18) ትዕዛዝን የሚሽሩ ሰዎችን የእግዚአብሔር ቃል

*(በገጽ 4 ይቀጥላል)*

## ወንድም ዊልያም

አንዲት ትንሽ የመጓጓዣ መርከብ በአየርላንድ የባህር ዳር ላይ ተሰበረች። የአደጋውን ጥሪ ሰምተው የመጡት የሕይወት አዳኝ ጓዶች «Life-saving crew» ከዚያች ትንሽ መርከብ ላይ የተረፉትን ሁሉ ወስደው መጓዝ ከጀመሩ በኋላ ዞረው ሲመለከቱ አስቀድመው ያላስተዋሉት አንድ ወጣት በተሰበረችው መርከቡ ላይ ተንጠልጥሎ አዩት። በዚህም ወቅት ከጓዶቹ አንዱ «ይህንን ምስኪን እናድነውን?» ሲል ሌሎቹን ጠየቀ «ሌሎቹም ማእበሉ እየበረታ ስለሆነ ቶሎ ከዚህ ቦታ መራቅ አለብን አለበለዚያ ሁላችንም እንጠፋለን ስለዚህ ሁላችን ከምናልቅ አንድ ሰው ቢሞት ይሻላል» አሉ። ተልእኮዋቸውን ጨርሰው ወደ ምድር ሲመለሱ አንድ ጎልማሳ እንዲህ ሲል ተናገረ «ከኔ ጋር አንድ ሰው በፈቃዱ የሚጓዝ ቢኖር ያንን ምስኪን ወጣት አድነዋለሁ» አለ። የዚህ ጎልማሳ እናት ከቡድኑ ጋር ነበረችና እጇን ትከሻው ላይ አድርጋ

*(በገጽ 7 ይቀጥላል)*

### በዚህ እትም ውስጥ

| | |
|---|---|
| «ሰው ሰራሽ ወግና ስርዓትን እያስተማረ በከንቱ ያመልከኛል» | 1 |
| ወንድም ዊልያም | 1 |
| ከአዘጋጆች | 2 |
| ሁሉን ትችላለህን? | 2 |
| ከአንባቢዎች | 2 |
| ክፍት የሥራ ቦታ በኢትዮጵያ | 3 |
| የኤድስ ቫይረስ የማይዛመትባቸው መንገዶች | 4 |
| የተዘጋው መጽሐፍ ሚስጢር ክፍል 2 | 5 |
| የመጨረሻው ማስጠንቀቂያ ክፍል 2 | 6 |
| የጥያቄዎ መልስ | 8 |

# ከአዘጋጆች



## ወንጌል

*የተወደዱ አንባቢ ሆይ!*

በዚህ ወር ከ2000 በላይ ከሚሆኑ አመታት በፊት በቤተልሄም የተወለደውን ሕጻን ልደት ምክንያት በማድረግ እነሆ የክርስቲያኑ አለም ይህንን በአል ለማክበር በመዘጋጀት ላይ ይገኛል። በዚህ የገና ወቅት ከተሞች ደምቀዋል። ስጦታ ለመግዛት፣ ቤቶቻቸውን ለማሸብረቅ፣ የተለየ የበአል ምግብ ለማዘጋጀት ብዙዎች በሩጫ ላይ ይገኛሉ።

በዚህ ወቅት ለገበያ በከተማ ውስጥ የሚራወጡትን ሰዎች ስንመለከት ለመሆኑ ስንቶቻችን ነን የአምላክ ሥጋ መልበስ ጥልቅ ትርጉም ገብቶን በቅርቡ ወደዚህች ምድር እንደ ሕጻን ሳይሆን እንደ ንጉሥ ሆኖ ዳግመኛ ሊመጣ ያለውን ጌታ በማሰብ እሱን ለመቀበል በመዘጋጀት ላይ የምንገኝ?። የጊዜያችን አንገብጋቢ ጥያቄ «ስንቶች ናቸው የሱስ ዳግም እንደሚመለስ የሚያምኑና ለዚያ መዘጋጀት እንደሚያስፈልጋቸው የተገነዘቡ?» የሚለው እንጂ የየሱስ መወለድ ታሪክ አይደለም።

ዝግጅት? አዎን ዝግጅት!። የገናን የምስራች ታሪክ ተረድተን ለበጉ ታላቅ ሠርግ እንድንዘጋጅ እግዚአብሔር ይፈልጋል። ለዚህ ሠርግ የምናደርገው ዝግጅትም፥ ልብሳችንን በበጉ ደም አጥበን ማጽዳት እና በየቀኑ በቅድስና ህይወት መመላለስ ነው። ጌታ ኃጢያተኛውን ልባችንን ወስዶ አዲስ ልብን ሊፈጥርልን ስለሚፈልግ ልባችንን ዛሬውኑ እንደገና እንስጠው።

የተወደዱ አንባቢ ሆይ! የጌታችን የየሱስ ክርስቶስን ወደዚህች ምድር መምጣት አለም ሁሉ በማስተዋልም ሆነ በዘልምድ በሚያስብበት በዚህ የገና ወቅት ለእርስዎም ሆነ ለእኛ የምንመኘው ነገር ቢኖር ጌታ ዳግም ሲመጣ «ኑ፣ እናንተ የአባቴ ብሩካን መንግሥትን ውረሱ» (ማቴ 25፣34) ከሚላቸው ወገኖች መካከል እንድንሆን ነው።

*የናንተው፥*
*ዳዊት መሐሪ እና ዳዊት መንግሥቱ*

## ሁሉን ትችላለህን?

ለሰው ይቅርታ አድርጎ መርሳት ቀላል አይደለም
ከኃጢያት መሸሽ በጣም ያስቸግራል፣
ነገርን ሁሉ ያለ ስህተት መስራት ከባድ ነው፣
ሁሉን ነገር አስቦ ማድረግ አስቸጋሪ ነው፣
በሁሉ ነገር ማመስገን ቀላል አይደለም፣
እውነትን ብቻ መናገር ያስቸግራል፣
ሁሉን በፍቅር ማየት በጣም ከባድ ነው፣
ራስን መግዛት የሚቻል አይደለም፣
የማይታየውን ማመን ቀላል አይደለም፣
ሁሉን በትዕግስት ማለፍ በጣም ይከብዳል፣
ለጋስ መሆን በጣም ያስቸግራል፣
ሁልጊዜ በጌታ መደሰት ቀላል አይደለም፣
ነገር ሁሉ ለበጎ ነው ማለት አስቸጋሪ ነው፣
ባልንጀራን እንደራስ መውደድ በጣም ይከብዳል፣
በእግዚአብሔር ብቻ መታመንና መመካት ቀላል አይደለም፣

አዎ! ሁሉን ነገር ማድረግ ቀላል አይደለም፣

«ነገር ግን ኃይልን በሚሰጠኝ
በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ»
(ፊሊ. 4፥13)

# ከአንባቢዎች

የጌታ የሱስ ክርስቶስን ቃል ለተራብን ሁሉ ቃሉን እንድትመግቡን ጌታ የመረጣችሁ ውድ የትንቢት ቃል አዘጋጆች በመጀመሪያ የከበረ ሰላምታዬን አቀርብላችኋለሁ። እኔ በስደት አለም መኖር ከጀመርኩ ወደ ስምንት አመት ሆነኝ። ይሄን ያክል አመታት ከጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ርቄና ጠፍቼ በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ስኖር ባለሁበት ፈልጎ ስላገኘኝ እጅግ በጣም ደስተኛ ነኝ። ቃሉንም እንድታስተምሩኝ፣መንገዱን እንድትመሩኝ፣ከጨለማ ወደ ብርሃን እንድታወጡኝ ጌታ የትንቢት ቃል መጽሔትን በእናንተ አማካኝነት ስለሰጠኝ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።

*ወ/ሮ አልማዝ አጥበው, ከሊባኖስ*

ለትንቢት ቃል አዘጋጆች! ሰላም፣ጤንነትና የጌታ ጸጋ በረከት ይብዛላችሁ። የአሸናፊው ጌታ ሠራዊቶች አይዞአችሁ በርቱ! ለእኔ ዶክተር የማይሰጥ ብርቱ ፍቱን መድኃኒት የትንቢት ቃልን አገኘሁ። ማንነቴን በትንቢት ቃል ውስጥ ስላገኘሁ ደስተኛ ነኝ። ከወገኖቼ ሕይወት ገጠመኝ በሕይወቴ ውስጥ ከሚያጋጥሙኝ ፈተናዎች እንድጠበቅና እንድጸና አድርጎኛል። ጌታ አሸናፊ ነው!

*እህታችሁ ሎሚነሽ ገ/ወልድ ከሊባኖስ*

<u>ውድ አንባቢያን!</u>
መጽሔታችን ወቅቱን ጠብቃ እንድትደርስዎ ማድረግ ስላልቻልን ይቅርታ እንጠይቃለን። ጌታ ጸጋውን ባበዛልን መጠን ወደፊት ይህንን ለማሻሻል እንሞክራለን። ጸሎታችሁ አይለየን። ***አዘጋጆች***



# ክፍት የሥራ ቦታ በኢትዮድያ

እንዴት ብዬ እንደምጀምር አላውቅም። ሆኖም በኢትዮጵያ ውስጥ ከምንግዜውም በላይ የወንጌል ሥራ እየተሠራ እንደሆነና በየትኛውም አቅጣጫ ሰዎች የአድቬንቲስትን መልእክት ለመስማት ክፍት የሆኑበት ጊዜ እንደሆነ ከምናየውና ከምንሰማው ዘገባ በመነሳት መመስከር እችላለሁ። በዚህ አጋጣሚ ግን በኛ በመሀከለኛው ኢትዮጵያ ሰበካ መስክ ስላለው እንቅስቃሴ ጥቂት ለማለት እወዳለሁ።

የመሀከለኛው ኢትዮጵያ ሰበካ ሰፊ የቆዳ ስፋት ያለው መስክ (ፊልድ) ነው። በስተሰሜን እስከ ወሎ ወልዲያ ድረስ፣በስተ ምእራብ እስከ ባኮ ድረስ፣በስተ ደቡብ ምእራብ እስከ ሚዛን፣በስተ ምስራቅ እስከ ሐረር ጅጅጋ ድረስ፣በደቡብ በኩል ደቡብ ፊልድን ተሻግረን በቀድሞው አጠራር ኩሉ ኮንታ በአሁኑ ጊዜ ግን የዳውሮ ዞንን ያጠቃልላል።

ለሥራችን እንዲያመቸን በማለት በሰባት ንኡስ ሰበካ (ዲስትሪክት) ከፋፍለናቸዋል

1) የዳውሮ ዲስትሪክት (ጨፌ)
2) የምስ. ኢትዮጵያ ዲሰትሪክት(ናዝሬት)
3) የምእራብ ሸዋ ዲሰትሪክት(አምቦ)
4) ወልቂጤ ዲሰትሪክት (ወልቂጤ)
5) ጁማ ዲሰትሪት (ጅማ)
6) ደሴ ዲሰትሪክት (ደሴ)
7) አዲስ አበባ ዲሰትሪክት (አ.አ)

እነዚህ የሥራ መስኮች በንኡስ ሰበካ የሥራ መሪዎች ይተዳደራሉ። እነዚህ የሥራ መሪዎች (District Leaders) ተጠሪነታቸው ለፊልዱ ሲሆን የፊልዱ ኮሚቴ አባሎች ናቸው። በጠቅላላው በፊልዳችን ውስጥ 102 አቢያተክርስቲያናት፣13 ትምህርት ቤቶችና 3 ክሊንኮች አሉን። እግዚአብሔር በታላቅ ክንዱ እየመራን ስለሆነ በውነቱ እርሱ እያደረገልን ያለውን በዚህ ጽሁፍ መዘርዘር አልችልም፣ከአሰብነው በላይ እየባረከን ነው። «አፍህን አስፋ እኔ እሞላዋለሁ» (መዝ 81፣10) ያለው ጌታ ራእዮቻችንን እውን ሲያደርግ አይተናል። እንግዲህ በቅደም ተከተል እግዚአብሔር የከፈተልንን የሥራ በር ለመዘርዘር ልሞክር፦

1ኛ. <u>ትምህርት ቤት፦</u> በመሀከለኛው ሰበካ ብቻ የት/ቤታችን ቁጥር ወደ 13 አድጎአል ከነዚህ ት/ቤ መሀከል በተለይ በዚህ አራት አመት ጊዜ ውስጥ የተከፈቱት አምቦ ቁጥር 1 እንደዚሁም ቁጥር 2። ጉደር፣ናዝሬት፣ደብረ ዘይት፣ወሊሶ አድቬንቲስት ት/ቤት በዳውሮ ዞን ገሳ ጨፌ እና ተርጫ ናቸው። እነዚህ ት/ቤቶች ከመዋእለ ህጻናት ጀምሮ ቀጣይነት ባላቸው መልኩ የተከፈቱ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በጣም በሚገርም ፍጥነት በመተሃራ የት/ቤት ህንጻ በማሰራት ላይ እንገኛለን። ነገሩ እንዲህ ነው፦ አንድ ቀን የመተሃራ ከተማ አስተዳዳሪዎች በላንድ ክሩዘር መኪና ቢሮዋችን ድረስ ይመጣሉ። ምን ይሉን ይሆን? ምን አስበው ይሆን? ከዚያ በቅርብ ጊዜ የከፈትናትን ቤ/ክ ዝጉ «ይህ አካባቢ የአፋር ብሄረሰብና የከረዩ ብሄረሰቦች መኖሪያ ስለሆነ እነሱ ደግሞ እምነታችሁን ስለማይፈልጉ ባስቸኩዋይ መዝጋት አለባችሁ» የሚሉን መስሎን ነበር። ነገሩ እንደዚያ አይደለም። ትህትና በተሞላው አነጋገር «እባካችሁ እኛ የአድቬንቲስት ት/ቤት በከተማችን እንዲከፈትልን እንፈልጋለን በከተማችን አንዳንድ ት/ቤቶች አሉ ሆኖም አኛ ከእግዚአብሔር በታች የናንተን ት/ቤት በዚህ ከተማ ተሰርቶ ልጆቻችን እዚያ ሲማሩ ማየት እንፈልጋለን። ለዚህም እንቅስቃሴያችሁ የምትፈልጉትን የመሬት ስፋት በምትፈልጉት ቦታ ላይ እንሰጣችኋለን። እኛ በሥራችሁ እንቅስቃሴ ላይ አብረናችሁ ነን። ድንጋይ እናቀርባለን አሸዋና ጠጠርም እናቀርባለን፣ገልባጭ መኪና እናዘጋጅላችኋለን በማንኛውም ልንተባበራችሁ ዝግጁ ነን። »

በጣም ተገረምን ዛሬ ዛሬ ደግሞ የምንለመንበት ጊዜ መጥቷል ያውም እስልምና ሃይማኖት በተስፋፋበት አካባቢ፤ይህን አይነቱን በእንቢታ መመለስ አልፈለግንምና ለጊዜው አስበንበት መልስ እንደምንሰጣቸው ነግረን ተለያየን። እኛ ምንም እንኳን በጀት የያዝንለት ባይሆንም ይህን ገፍቶ የመጣውን ፍላጎት የህዝቡን ራእይ ማጨለም ስላልፈለግን ከዚህም ከዚያም ብለን ከከተማው ህዝብ ጋር በመቀናጀት ዛሬ በሰጡን 16ሺ ካሬ ሜትር መሬት ላይ የት/ቤት ህንጻ ግንባታ እያካሄድን ነው። በዚህ አጋጣሚ ሳላመሰግን የማላልፈው ሰው አለ፤ይኸውም አቶ አለሙ ኀበዜን ይሆናል። በሳቸው ጥረት በተላከልን ገንዘብ የመተሀራን ቤ/ክ ሰራን። ይህም ለዚህ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ፈር ቀዳጅ ሆንዋል።

ስለ ትምህርት ቤታችን የህንጻ ግንባታ ብቻ ተናግሬ ማቆም አልፈልግም በነዚህ ት/ቤቶቻችን ውስጥ የሰው ግንባታም ይካሄዳል፤ በተለይም በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶቻችን አማካይነት ብዙ ነፍሳት ወደ ቤ/ክ እየተጨመሩ ነው። ተማሪዎችን ብቻ ሳይሆን አስተማሪዎችንም ይጨምራል። ለምሳሌ ለመጥቀስ ያህል በአቃቂ አዴቬንቲስት ት/ቤት በዚህ አመት ብቻ (እ.ኢ.ት.አ.1996) 42 ተማሪዎች ተጠምቀዋል። የቀበና አዴቬንቲስት ት/ቤት እስከ 10ኛ ክፍል ደርሶዋል ወላጆች ት/ቤቱ እስከ preparatory (ለዩኒቨርስቲ ቅድመ ዝግጅት) እንዲያድግ ከፍተኛ ግፊት ያደርጋሉ ምክንያቱም የቀበና አዴቬንቲስት ት/ቤት በቀለም ትምህርት በኩል ተወዳዳሪ የለውም። ተማሪዎች በከፍተኛ ውጤት ያልፋሉ፤ ወዳቂ የሚባል ነገር ተሰምቶ አይታወቅም። ባለፈው አመት አንድ ሁለት ፎቅ ከፍታ ያለው 12 የመማሪያ ክፍሎች ያሉትን ህንጻ ግቢ ውስጥ አሰርተናል፤ ሆኖም ያም የተማሪውን ፍላጎት አላሟላም። ለአዲስ አበባ መሬት አስተዳደር ሌላ ሰፋ ያለ መሬት እንዲሰጠን ጠይቀናል ከተሰጠን በሌላ ስፍራ ሁለተኛ ደረጃ ማለትም ከዘጠነኛ እስከ ፕሪፓራቶሪ ድረስ ለመክፈት የረዥም ጊዜ እቅድ ይዘናል።

2ኛ. <u>ክሊኒክ</u> በመሀከለኛው ኢትዮጵያ ሰበካ ሶስት ክሊኒኮች አሉን ሁለቱ ቀደም ሲል የተሰሩት የእንጦጦ (ራስ ካሳ) ክሊንክና የፌሳ ክሊንክ ናቸው። በአለፈው አመት ተጀምሮ ተጠናቆ በዚህ አመት ሥራ የጀመረው በወልቂጤ ዲስትሪክት ልዩ ስሙ «ጩመሌ» በተባለ አካባቢ ዘመናዊ ክሊኒክ ተከፍቷል። አቶ አለነ ተረፈና አቶ ይረጋል ሲሳይ ወገኖችን አስተባብረው ገንዘብ በመላክ ከፍተኛ አስተዋጽዎ አድርገዋል፤ ጌታ ይባርካቸው ሰማለት እወዳለሁ። በእነዚህ ለጋሽ ወገኖችና የመሀከለኛ ሰበካ ቅንጅት ሊሰራ ችሏል። ይህ ክሊኒክ በተለይም አካባቢውን እያጠቃ ካለው የወባ በሽታና ካንዳንድ ወረርሽኝ በሽታዎች ለመከላከል ከፍተኛ አውተዋጽዎ ይያደረገ ነው። በክሊኒኮቻችን ሁሉ ጠዋት ጠዋት ስራ ከመጀመራቸው በፊት ወንጌላውያን በስፍራው ተገኝተው ለበሽተኞች አጠር ያለ ቃል አካፍለው ጸሎት ያደርጉላቸዋል።

3ኛ. <u>ቤተ ክርስቲያናትና የወንጌል እንቅስቃሴ</u> በአንድ መጽሐፍ ላይ ያነበብኩት «We are in the soul winning buisness» ይላል። አዎን ዋናው አላማችን ሰፍሳትን የማዳን ጉዳይ ነው። ት/ቤቶቻችን፣ክሊኒክ፣ሌላም ድርጅቶቻችን በሙሉ አላማቸውን ካልዘነጉ ነፍሳትን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ማምጣት ነው። 2004 ዓ.ም. የወንጌል ዓመት (Year of Evangelism) በመባል ይታወቃል ስለዚህ ብዙ የወንጌል ጥረቶች እናካሂዳለን፤ብዙዎች ጌታን ይቀበላሉ፣ ብዙ አዳዲስ ስፍራዎች ገብተናል ይህም የቤ/ክንን ቁጥር እያሳደገ ነው፤ በተለይም በአንቦ ዲስትሪክት በቅርቡ ስለሆነው አንድ አስደናቂ ነገር ትንሽ ላውጋችሁ፦

ለብዙ አመታት ብዙ ምእመን ወዳለበት ወልቂጤ ዲስትሪክት ስንሄድ በወሊሶ ከተማ እያለፍን እንሄዳለን «እባካችሁ አትለፉኝ» ያለች ይመስል ይኸው ዛሬ በወሊሶ ከተማ ት/ቤት፣ቤ/ክን ተሰርቶ ጥሩ እንቅስቃሴ እየተካሄደ ነው። በቅርቡ በወሊሶ ከተማ የመንግሥት አዳራሽ ተከራይተን ታላቅ ክሩሴይድ አካሂደናል። ቁጥሩ ከ2000 የማያንስ ህዝብ በየምሽቱ መልእክታችንን ለመስማት ይመጡ ነበር። በዚያ ፕሮግራም ጌታ ብዙ ነፍሳትን ሰጠን፤ይህ ፕሮግራም ለቤ/ክን ምእመናን ታላቅ የመነቃቂያ ጊዜ ነበር በዚያ መንፈስ እንዳሉ በአቅራቢያቸው ወዳሉ አጎራባች ከተማዎች የወንጌል ስርጭት ጀመሩ በቅርቡ ተጠማቂዎችን አዘጋጅተው ሰማጥመቅ ሄጄ እጅግ በጣም ተደስቼ መጣሁ። ከተለያዩ

*(በገጽ 7 ይቀጥላል)*



## ጤናችን

# የኤድስ ቫይረስ የማይዛመትባቸው መንገዶች

የኤድስ ቫይረስ በማናቸውም አይነት ነፍሳት ማለትም በትንኝ፣ ትኋን፣ ቁንጫና ቅማል በመሳሰሉት ንክሻ አይተላለፍም። እንዲሁም በመሳሳም፣ በመጨባበጥ፣ በአንድ ቦታ አብሮ በመኖር፣ አብሮ በመብላት፣ በትንፋሽ፣ በንጥሻ፣ መጸዳጃ ቤት ወይንም የዋና ገንዳ በሕብረት በመጠቀም፣ በምግብና በውኃ አይተላለፍም።

አንድ በሽተኛን ማስታመምና መንከባከብም ለቫይረሱ አያጋልጥም። ይሁን እንጂ ለአንድ በሽተኛ እንክብካቤ በሚሰጥበት ወቅት በተለይ በአካል ፈሳሹ የተበከለን ልብስ ከመንካት በፊት የእጅ ጓንት መጠቀም ያለበለዚያም እርዳታ ከተሰጠ በኋላ እጅን በሳሙና በሚገባ መታጠብ ያስፈልጋል።

***ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን መከላከል ይቻላል!!***

በግብረ ሥጋ ግኑኝነት፣ ከእናት ወደ ልጅ እንዲሁም በተበከለ ደም አማካኝነት የሚተላለፍ ኤች.አይ.ቪን መከላከል ይቻላል። በዚህ መስክ የሚሰጠው የምክር አገልግሎትም የአንድ ሰው ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ያለውን በቂ ግንዛቤና እውቀት እንዲያዳብር ከመርዳቱ ሌላ በሽታውን ለመከላከልና ሒደቱን ለመቆጣጠር ታላቅ አስተዋጽኦን ያደርጋል።◆ *አዘጋጆች*

---

***«ሰው ሰራሽ ወግና...»*** *(ከገጽ1 የዞረ)*

በማቴ 5÷18፤19 ማስጠንቀቁን እያወቀች የካቶሊክ ቤተክርስቲያን በ336 ዓ.ም. ላዶቂያ ላይ ባካሄደችው ጉባኤ ከአሕዛብ ጋር በመተባበር የራሷን ከፍ ብሎ የመታየት ተልዕኮ ለማስፈፀም እንዲመቻት ስትል የቅዳሜን ሰንበትነት ሽራ እሁድ በሰንበትነት እንዲከበር/እንዲጠበቅ መወሰኗን ታሪክ ያረጋግጥልናል። የአብዛኛው የክርስቲያን ክፍል እሁድን በሰንበትነት የመከተል ልማድ መነሻውም ይኸው ነው። «ሰው ሰራሽ ወግና ስርዓትን እንደ ሕግ አድርጎ እያስተማረ በከንቱ ያመልከኛል» ይላል የጌታ ቃል።

**የገና በዓል/Christmas**

የክርስቲያኑ አለም በአሁኑ ዘመን እንደ እምነት መስመሩ በየአመቱ ዲሴምበር 25ን ወይም ጃንዋሪ 7ን በልደት በዓልነት ያከብራል። እስከ 4ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ በኢየሱስ መወለድ የእግዚአብሔርን መገለጥ ምክንያት በማድረግ ክርስቲያኖች ጃንዋሪ 6ን ያከብሩ እንደነበር መረጃዎች ያመለክታሉ። ሆኖም በአብዛኛው የአህዛብ ክፍል በከፍተኛ ድምቀት ለዘመናት ይከበር የነበረው የኃያሉ ፀሐይ ክብረብዓል ("Festival of the unconquered Sun"/Saturnalia) እለት ዲሴምበር 25 በሮም መንግስት ትዕዛዝ እንደ ጌታ ልደት ቀን አድርጎ መላው የግዛቱ ሕዝብ ቀስ በቀስ እንዲቀበለውና እንዲያከብረው ተፅዕኖ እየተደረገበት መጣ።

ይህ ከኃያሉ ፀሐይ ጋር የተያያዘው የባዕድ አምልኮ ከክርስትና እምነት ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌሌው ግልፅ ሆኖ ሳለ ከክርስትና ጋር ለማዛመድ የሚደረገው ጥረት ደግሞ የሚገርም ነው። ሰዎች ሚልክያስ 4ን እንደማስረጃ በመጠቀም «ክርስቶስ የፅድቅ ፀሐያችን» ነውና በማለት ከአሕዛብ የፀሐይ አምልኮ ጋር በማያያዝ አሕዛብን ወደ ጌታ ለማቅረብ በሚል ሰበብ ቃሉ ሲጣመም እናያለን። ይህንን ጥቅስ ከላይ የተነጋገርንበትን የእሁድ ሰንበትነትንም ለማረጋገጥ ሲጠቅሱት «ክርስቶስ የተነሳውም በእሁድ ቀን/የፀሐይ ቀን (Sunday) ስለሆነ ክርስቶስ ፀሐያችን ነውና እሁድ የጌታ ቀን ነች» ለማለት ሰዎች ይዳዳቸዋል። ይህ ደግሞ ቃሉን ሊለው የማይፈልገውን በግድ የማሰኘት ያህል ነው።

በኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ደምና በሐዋርያት መስዋዕትነት የተገነባችውን ቤ/ክርስትያን ከባዕድ አምልኮ ምንጭ ጋር ማዳቀል/መበረዝ እንደማይገባ በማመናቸው ምክንያት ይህ የተሳሳተ አመለካከት በአርመኒያ፤ በአለክሳንደሪያና በኢትዮጵያ ይገኙ በነበሩ ቤ/ክርቲያኖች በኩል ተቀባይነት እንዳላገኘ ኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካ ያስረዳል። በዚህም ምክንያት ነው በነዚህ አገሮችና በኋላም የእነሱን የእምነት መስመር በተከተሉ አገሮች የሚኖሩ በተለይ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዲሴምበር 25 ሳይሆን ጃንዋሪ 7 በየአመቱ በጌታ የልደት ቀንነት የሚከበረው።

በሰው ሕግና ወግ አስገዳጅነት የተገነባው ዲሴምበር 25ን የማክበር ልማድ በአሁኑ ዘመን በአብዛኛው የአለም ክፍል በተለይ በምዕራቡ ዓለም እንደ ትክክለኛ የጌታ ልደት ቀን ተቆጥሮ በከፍተኛ ድምቀት በየአመቱ ሲከበር ይታያል።

የዚህ ጽሑፍ መልዕክት የጌታን ልደት ማክበር የለብንም የሚል አይደለም። ይልቁንም ወደትክክለኛው መስመር የሚጠቁም ሀሳብ ያዘለ መልዕክት ነው። ይህም ማለት ስለዚህ ጉዳይ ከተነሳና ቀኑ መከበር አለበት ከተባለ ትክክለኛው የልደት ቀን እንጅ (ምንም እንኳን መቶ በመቶ ስለ ትክክለኛው እለት እርግጠኞች ባንሆንም) በሰው ሕግና ወግ አስገዳጅነት የተሰየመው የባዕድ አምልኮ መነሻነት ያለው ዕለት መሆን እንደሌለበት ለማስገንዘብ ነው።

**የገና አባት/St.Nicholas (Santa Claus)** ቅዱስ ኒኮላስ በደግነቱ የታወቀና በአሁንዋ ቱርክ በ4ኛው ክፍለ ዘመን የሚራ ጳጳስ በነበረበት ወቅት በንጉስ ዲኦክሌቲያን ስደት የገጠመው ሰው እንደነበር ይነገርለታል። ደግነት የአንድ እውነተኛ ክርስቲያን የእለት ተእለት ባህሪ ሆኖ እያለ በአመት አንድ ጊዜ ብቻ እንደሚከናወን ተቆጥሮ "በገና አባት" ተመስሎ የበለፀገው ባህል ከልደት በዓል ጋር የሚያያይዘው ምክንያት የለም። በዚህ ባህል መሰረትም እየተከበረና እየተመለከ ያለው ቅዱስ ኒኮላስ እንጅ ጌታ ኢየሱስ አለመሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል። በርግጥ የምናመልከው አምላክ የሰጦታዎች ምንጭ መሆኑን ለማመልከት ይህንን ልምድ እንደሚጠቀሙበት የሚጠቅሱ ሰዎች አሉ። ይሁን እንጃ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ሲሰጠን እኛ ይህን ክቡር ስጦታ ለማድነቅ የምንችለው እርስ በርሳችን የውለታና የጥቅም ስጦታ በመለዋወጥ ሳይሆን በየለቱ ራሳችንን በመስጠትና የልግስና ሕይወትን በሰውና በእግዚአብሔር ፊት በመኖር ነው።

**የገና ዛፍ/Christmas Tree**

ከገና ዛፍ ጋር የተያያዘው ባህል ወደ እንግሊዝ አገር ለመጀመሪያ ጊዜ የገባው በ19ኛው ክፍለ ዘመን የንግስት ቪክቶሪያ ባለቤት በነበረው በልዑል አልበርት አማካኝነት ነው። በቅድመ ክርስቲያን ዓመታት/ዘመናት የጀርመን አገር ሕፃናት ለባዕድ አማልዕክት ሕያው መስዋዕት ሆነው ይቀርቡ የነበሩት በኦዲን ዋርካ/"Oak of Odin" ስር ነበር። ጀርመን ክርስትናን ስትቀበል ይህ ዛፍ በማይሞተው የሕይወት ዛፍ በክርስቶስ ተመስሎ ቀረበ። የሰው ልጅ ከባዕድ አምልኮ ሳይላቀቅ እምነቱን እንደሚለዋውጥ ይታያል። የያዕቆብ ሚስት ራሔል ያባትዋን ጣዖቶች ሰርቃ የተጓዘችው (ዘፍ 31÷32–35) ደሟ ውስጥ ለዓመታት ከተዋሃደው የባዕድ አምልኮ ልማድ መላቀቅ አቅትዋት ነበር። ዛሬም በዘመናችን በእውነት የተለወጥን እየመሰለን የጥንቱን ከንቱ ልምድና ወግ በልባችን ጓዳ አቅፈን እንደምንጓዝ የእውነት ብርሃን ያጋልጠናል።

**የገና መብራት/ሻማ/Candle light**

በጀርመን ከተጀመረው የገና ዛፍ ባህል ጋር ተያይዞ ያበበው የገና ሻማ ባህልም መነሻው በጥንታዊትዋ ቅድመ ክርስቲያን ሮማ ከዲሴምበር 21 እስከ 25 ድረስ አመታዊውን የኃያሉ ፀሐይ ክብረ በዓል ምክንያት በማድረግ ሕዝቡ ሻማ ያበሩ ከነበረው ባህል መሆኑን ታሪክ ያስረዳል።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ከልደት ጋር የተያያዙ ሀሳቦች በግልፅ የሚያስገነዝቡት ብዙዎቹ የክርስትና ባህሎች ከባዕድ አምልኮ የተገኙ መሆናቸውን ነው። እጅግ በጣም የሚያሳዝነው ብዙ ክርስቲያኖች በባዕድ አምልኮ ላይ ለተገነባው የምዕራቡ ዓለም ባህል በዕምነት ስም ራሳቸውን ማስገዛታቸው ነው። ከልደትና አጅበውት ከበለፀጉት ከገና ዛፍ፤ ከገና ሻማና ከገና አባት ጋር የተያያዘ ባህል ሁሉ ለክርስትና እምነት መሰረት ባዕድ ነው። "የበግ ለምድ" ለብሶ የመጣን የባዕድ አምልኮ በምንም ሁኔታ ከክርስትና እምነት ጋር በማዳቀል ማስተናገድ ተገቢ አይደለም። የቄሳር ለቄሳር የእግዚአብሔር ደግሞ ለእግዚአብሔር ይሁን (ማር 12÷17)። ንጉሥ ሳኦል በራሱ ግንዛቤና ሀሳብ ተመርቶ እግዚአብሔርን ለማስደሰት

*(በገጽ 5 ይቀጥላል)*

# የተዘጋው መጽሐፍ ሚስጢር ክፍል 2 (ራእይ 6)

**ተከታታይ ትምህርት**



ባለፈው ጥናታችን እንደተመለከትነው ራእይ ምእራፍ አምስት ያሳየን በመላው የምድር ታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔርን አመራር፣ የመንግሥታትንና የአብያተ ክርስቲያናት ትንቢታዊ ታሪክ እንደዚሁም የየአንዳንዱን ግለሰብ የግል ታሪክ በሰማይ ቁጥጥር ስር እንዳለ ነበር።

በዚህ ጥናታችን የምናየው የታሪክ ክፍል ደግሞ ክርስቶስ ማህተሙን ሲከፍት የሚከሰተውን ነው። ይህንም በሚሆንበት ጊዜ በአንዳንዶች ላይ የሐቅ ፍርድ ሲገለጽ ለሌሎች ደግሞ የታረደው በግ ምህረት ይገለጽላቸዋል። ማለትም አንዱ ወገን ሲድን ሌላው ደግሞ ይጠፋል።

### አራቱ ፈረሶች ምንን ያመለክታሉ?

ኢየሱስ ማህተሙን ሲከፍት አራት ፈረሶችን እናያለን። እነዚህ የምን ምሳሌዎች ናቸው? በመጀመሪያ ልንገነዘው የሚገባው መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መላው አለም ሲናገር አራቱን የምድር አቅጣጫዎች በማስመልከት ማለትም ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምስራቅና ምእራብ እያለ ያስረዳል። ባለፈው ጥናታችን እንደሚያስታውሱት አራቱ ሕያዋን ፍጡራን በአራቱ የምድር ማእዘናት ላይ ስልጣን አላቸው። በሰዎች ታሪክም ሂደት ከበስተጀርባ ሁነው እንዲሰሩ ኃይል አላቸው። ስለዚህ እዚህ ላይ የአራቱ ፈረሶች መገለጽ ትክክለኛ ጊዜው ነው።

ፈረሶች አራቱን የሰማይ መናፍስት ወይንም አራቱን ነፋሳት ያመለክታሉ ይባላል። እነዚህም የሁሉን ገዥ ከሆነው ከእግዚአብሔር ዙፋን ይነሳሉ (ዘካርያ 6.5) እግዚአብሔርም እነዚህን ፈረሶች «ወደ ምድር ሁሉ ሂዱ ተመላለሱባትም» ይላቸዋል (ዘካርያ 6,7)። በራእይ 7,1-3 የእግዚአብሔር ሕዝብ ማህተሙን እስከሚቀበል ድረስ የምድርን አራቱን ነፋሳት የያዙ አራት መላእክት እንዳሉ እናያለን። የእግዚአብሔር ሕዝብ ማህተሙን ከተቀበለ በኋላ ነፋሳቱ ይለቀቃሉ። ያኔም ታላቅ ጥፋትና ሃዘን በምድር ላይ ይወድቃል።

በራእይ ምእራፍ 6 ላይ ያሉት አራቱ ፈረሶችና በምእራፍ 7 ላይ ያሉት አራቱ ነፋሳት የሚያመለክቱት አብዛኛው ተመሳሳይ ነገር ሲሆን አንድ በሁለቱ መሀል ያለ ልዩነት አራቱ ፈረሶች የሚያመለክቱት የምህረት ጊዜ ለሰው ልጆች ከማለቁ በፊት የሚፈጸመውን ሲሆን አራቱ ነፋሳት ደግሞ የምህረት ጊዜ ካለቀ በኋላ የሚከሰተውን ነው። አራቱ ፈረሶች ቤ/ን ያሳለፈችው ልምዱዋንና ሰይጣን ቤ/ንን ለማጥፋት ጥረት ሲያደርግ በምድር ላይ የተከሰተውን ሰቆቃ ሲሆን አራቱ ነፋሳት ደግሞ የሚያሳዩት የወንጌል ሥራ ተሰርቶ ሲያልቅና የእግዚአብሔር መንፈስ ተይዞው የነበሩት ነፋሳት እንዲለቀቁ ሲያደርግ የሚከሰተውን ነው።

### የመጀመሪያው ማህተም፦ ነጭ ፈረስ ራእይ 6፥1-2

ነጭ ፈረስና ጋላቢው የሚያመለክቱት የመጀመሪያዋን የሐዋርያት ቤ/ን ሲሆን ይህች ቤ/ን የሰዎችን ልብ ወደ ክርስቶስ ወንጌል በመማረክ የወንጌል እውነትና የክርስቶስን ጽድቅ ታስተምር ነበር በመዝሙር 51፥7 እና በኢሳያስ 1፥18 ላይ ነጭ ምንን እንደሚያመለክት ያሳየናል።

ጋላቢው በእጁ የያዘው የሚያሳየው ወደ ክርስቶስ ተከታዮች ልብ ውስጥ ሰርጾ የሚገባውን የእግዚአብሔርን ጥበብ እውቀት ነው። ወንጌልን የሚቀበሉ ጥፋታቸው ማለትም ኃጢአታቸውን ተቀብለው አዳኝ እንደሚያስፈልጋቸው ዳዊት በመዝሙር 38፥21 ላይ እንዳለው ይገነዘባሉ። በጋላቢው ራስ ላይ ያለው አክሊል የሚያመለክተው በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የሚያንጸባርቀውን የእግዚአብሔርን ግርማ ነው። (ኢሳያስ 28፥5 ኢሳያስ 62፥3)

እንግዲያስ የመጀመሪያው ማህተም መፈታት የሚገልጸው በክርስቶስ ስም ድል እየነሳች የነበረችውን የክርስቲያን ቤ/ን የመጀመሪያ ታሪክ ነው።

### ሁለተኛው ማህተም - ቀዩ ፈረስ ራእይ 6፥3-4

ድል ይነሳ የነበረው ነጭ ፈረስ እንደ ደም በቀላው በቀዩ የስደት ፈረስ ተተካ። አዎን በርግጥ ክርስቶስ የሰላም ልዑል ቢሆንም (ኢሳያስ 9፥6) የክርስቶስ ወንጌል በምድር ላይ መሰበክ ግን ማቴዎስ 10፥34 ላይ እንደተጠቀሰው የወንጌል ተቀዋሚዎች ወንጌልን የተቀበሉትን ለማጥፋት ቤ/ንን በማሳደድ ሰላምን ያናጋሉ። የክርስቲያን ቤ/ን በተጀመረች በአጭር ጊዜ ውስጥ ትሰደድ ጀመር። የክርስቶስ ተከታዮች ከእምነታቸው የተነሳ በጣም ይሰቃዩ ጀመር። የሮም መንግሥት ክርስትና ወደ ድንበሩ እንዳይደርስ ብሎ የብዙ ክርስቲያኖችን ደም አፈሰሰ። እንግዲህ ቀዩ ፈረስ የሚያመለክተው ቤ/ን በሁለተኛው በሶስተኛውና በአራተኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የደረሰባትን ስቃይና ስደት ነው።

### ሶስተኛው ማህተም - ጥቁሩ ፈረስ ራእይ 6፥5-6

ሶስተኛው ማህተም ሲከፈት የጥቁሩን ፈረስ ማለትም መንፈሳዊ ጨለማ የሰፈነበትን ጊዜ እናያለን። ይህ በአራተኛው፣ በአምስተኛው ከዚያም ስድስተኛውን ክፍለ ዘመን የወረረውን መንፈሳዊ ጨለማ የቤ/ን ታሪካዊ ውድቀት ያሳያል። ይህ ጊዜ የታላቅ የሞራል ውድቀት፣ ቤ/ን እውነተኛውን የክርስቶስ ትምህርት ያዛባችበት ጊዜ ነበር። በሙሉ ልባቸው ወንጌልን ያልተቀበሉ ብዙ ሰዎች (አህዛብ/ፓጋንስ) ወደ ቤ/ን ገቡ። እነዚህ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ባህሪ ያላቸው አመለካከት ትክክለኛ ካለመሆኑም ሌላ በመንፈሳዊ ምንዝርናና በስልጣን ሽሚያ ልባቸው ተወጥሮ ተይዞ ነበር።

ጥቁሩን ፈረስ የሚጋልበው ሰው በእጁ በያዘው ሚዛን ላይ የተመዘነው ጥቂት ምግብና በሌላው አንጻር ደግሞ ብዙ ገንዘብ የሚያሳየው በቤ/ን ላይ አንሰራፍቶ የነበረውን ታላቅ መንፈሳዊ ረሀብ ነበር። ነቢዩ አሞጽ ይህንን ሲያንጸጽር እንዲህ ይላል፦ «አሞጽ 8፥11»። በዚህ ወቅት ነፍሳት ንጹሁን የሰማይ ዳቦ ለመመገብ ታላቅ ጥማት ነበራቸው። የወንጌል እውነት ግን በቀላሉ የማይገኝ ሆነ። የሃሰት ትምህርት ግን ተስፋፋ። ቢሆንም ግን ከአምላክ ቸርነት የተነሳ «ዘይቱንና ወይኑን አትጉዱ» የሚል ትእዛዝ ተሰጠ። ዘይት በመንፈስ ቅዱስ የመቀባት ምልክት ነው። ወይን ደግሞ በክርስቶስ ደም የመዋጀት ምልክት ነው። በዚህ በጥቁሩ ፈረስ በተመለከተው የመንፈስ ረሀብ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ የተቀቡ ንጹሁን የወንጌል እውነት ያላዳቀሉ ነፍሳትም ነበሩ።◆ *ይቀጥላል*

---

*«ሰው ሰራሽ ወግና...» (ከገጽ 4 የዞረ)*

በሚል ሰበብ ያልተፈቀደለትን ምርኮ ይዞ በመገኘቱ ከተሰጠው የመሪነት ቦታ/ክብር እንደ ተነሳ ቃሉ በ1ኛ ሳሙ 15፥10–23 በአፅንኦት ይነግረናል።

ጌታ ዳግም ሲመጣ በሕይወታችን እንዳከበርነውና እንደታዘዝነው የምናረጋግጠው ሰው ሰራሽ ወግና ስርዓትን እንደ ሕግ አድርገን በማስተማር/በመከተል ሳይሆን እንደ ቃሉ መኖር ስንችል ብቻ ነው። ምንም እንኳን ይህን ሁሉ የረዥም ዘመን ልምዳችንን ለመጣልና በዙሪያችን ካለው ሕብረተሰብ መገለል ቀላል ሊሆን ባይችልም መቀረጥ ያለባቸው ነገሮች ሁሉ እያመመንም ቢሆን መቀረጥ አለባቸው። ይህ ደግሞ በፀጋው ውስጥ ላለን ጌታን እንደምንወደው ለምንናገር ሁሉ የሚቻልና ከፍቅር የተነሳ ማድረግ ያለብን ጉዳይ ነው።◆

*ፀጋዓለም ያለው, ከኖርዌይ*





# የመጨረሻው ማስጠንቀቂያ (ክፍል 2)

(ከታላቁ ተጋድሎ ምዕ.38)

*ውድ የትንቢት ቃል አንባቢያን፥ ካለፉት እትሞች ጀምሮ «The Great Controversy» ወይም «ታላቁ ተጋድሎ» ከሚለው መጽሐፍ ውስጥ የመጨረሻዎቹን ሰባት ምእራፎች በተከታታይ በማቅረብ ላይ ነን። ይህ መጽሐፍ በ19 መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ እና በ20 መቶ ክ.ዘ. መጀመሪያ ላይ በ ኤለን ጂ ኋይት የተጻፈ ሲሆን ወቅታዊ እውነትን የያዘ በመሆኑ ለአንባቢያን በረከት ይሆናል ብለን እናስባለን።•*

ተጋድሎው ወደ አዳዲስ መስኮች እየተስፋፋ ሲሄድና የሰዎችም ልብ (ሃሳብ) በእግር ወደ ተረገጠው የእግዚአብሔር ሕግ ሲያመራ፤ ሰይጣን ይቆጣል (ይሸበራል)። በመልእክቱ ውስጥ ያለው ኃይል መልእክቱን የሚቃወሙትን ብቻ ያስቆጣል። መንፈሳዊ መሪዎች (ካህናቶች) በመንጎቻቸው ላይ ብርሃን እንዳይበራ ለማድረግ እጅግ ከሰው አቅም በላይ በሆነ ኃይል ይጥራሉ። በተቻላቸው መንገድ የዚህን ጠቃሚ ጥያቄ ውይይት በትእዛዛቸው ለማጥፋት ይጥራሉ። ቤተ ክርስቲያን ጠንካራ የሆነው የመንግሥት ኃይል ጉዳይዋን እንዲያስፈጽምላት ትጠይቃለች (ጥሪ ታቀርባለች)፣በዚህ ሥራም የካቶሊክ እና የፕሮቴስታንት ቤ/ክ (ሉተራንስ) ይተባበራሉ። እሁድ ይከበር ዘንድ ግዳጅ እንዲወጣ በመጣር ላይ የሚገኘው እንቅስቃሴ ይበልጥ ጉልህና ድፍረታዊ እየሆነ ሲመጣ፣የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በሚጠብቁት ላይ ሕጋዊ እርምጃ ይወሰድ ዘንድ ጥሪ ይተላለፋል።

የእግዚአብሔርን ሕግ የሚጠብቁት በገንዘብ ወይም በእስር እንደሚቀጡ በማስጠንቀቅ ያስፈራሩዋቸዋል። ለአንዳንዶቹ ደግሞ እምነታቸውን ከተው ስልጣን ያለበትን ስፍራ፣ስጦታና ጥቅም እንደሚያገኙ ቃል ይገቡላቸዋል። የእነዚህ የእግዚአብሔር ባሪያዎች የማይለወጥ መልስ ግን «ስህተታችንን በእግዚአብሔር ቃል ተደግፋችሁ አሳዩን» የሚል ይሆናል። ይህ አባባል ማርቲን ሉተር በተመሳሳይ ሁኔታ በነበረ ጊዜ ካቀረበው ጥያቄ ጋር አንድ ነው። ተወንጅለው በፍርድ ቤት የቀረቡት ሰዎች ስለ እውነት የማያወላውል ምስክርነት ይሰጣሉ። እነርሱን የሚያደምጡ አንዳንዶችም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በሙሉ ለመጠበቅ አቋም ይወስዳሉ። በመሆኑም እውነትን በሌላ መንገድ ለማወቅ የማይችሉቱ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሰዎች የእውነት ብርሃን ይበራላቸዋል።«»

በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል በቅን መታዘዝ እንደአመጽ ይታያል። ልባቸው በሰይጣን ስለታወረ ወላጆች በጌታ ቃል በሚያምነው በገዛ ልጃቸው ላይ የጭከና ድርጊት ይፈጽማሉ። ጌቶች የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የሚጠብቁትን አገልጋዮቻቸውን ይጨቁናሉ፤ፍቅርም ትቀዘቅዛለች። ልጆች የወራሽነት መብታቸውን ተገፈው ከቤታቸው ይባረራሉ። የጳውሎስ ትንቢት ቃል በቃል ይፈጸማል «በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ» (2ኛ ጢሞ 3፥12)። ስለእውነት የቆሙት ክርስቲያኖች እሁድን በሰንበትነት ለማክበር ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ሲገልጹ አንዳንዶቹ ወደ ወህኒ ቤት ይከተታሉ፣አንዳንዶቹ ይሰደዳሉ፣ሌሎቹ ደግሞ እንደባሪያዎች ይቆጠራሉ። ይህ ሁኔታ ይፈጸማል ብሎ ለማመን ያስቸግር ይሆናል፤ነገር ግን ይህ ሁሉ እንዳይሆን ለጊዜው የሚያግደው የእግዚአብሔር መንፈስ ከሰው ሁሉ በሚወሰድበትና ሰው ሁሉ የእግዚአብሔርን ሕግ በሚጠላው በሰይጣን ቁጥጥር ስር ሲሆን እንግዳ ነገሮች ይከሰታሉ። ፈሪሃ እግዚአብሔርና የእግዚአብሔር ፍቅር ከሰዎች ልብ ሲርቁ የሰው ልብ ጨካኝ ሊሆን ይችላል። ማእበሉ እየተቃረበ ሲመጣ «በሶስቱ መላእክት መልእክት እናምናለን» ብለው የተናገሩት፣ነገር ግን ለእውነት በመታዘዝ ያልተቀደሱት ክርስቲያኖች አቋማቸውን ትተው በተቃራኒው (በተቃዋሚው) ወገን ይሰለፋሉ። ከዓለም ጋር አንድ በመሆንና ከዓለማዊ መንፈስ ጋር በመተባበር ነገሮችን በተመሳሳይ ብርሃን ይመለከታሉ። ፈተናም ሲመጣባቸው ቀላሉንና በሰዎች ሁሉ የተወደደውን ጎን ይመርጣሉ። መልካም ስምና ተውህቦ ያላቸው በአንድ ወቅት በእውነት ሃሴት ያደርጉ የነበሩ ሰዎች ኃይላቸውን ነፍሳትን በማታለልና ወደ ተሳሳተ ጎዳና በመምራት ሥራ ላይ ያውሉታል። የቀድሞ ወንድሞቻቸውም ብርቱ ጠላቶች ይሆናሉ። ሰንበትን የሚጠብቁ ምእመናን በእምነታቸው ምክንያት በፍርድ ፊት መልስ ለመስጠት በሚቀርቡበት ጊዜ የእነርሱን ጉዳይ በተመለከተ አሳሳች ነገር በማቅረብና በመወንጀል፣የሀሰት ዘገባና ትክክለኛ ያልሆነ ሪፖርት በማቅረብ ገዢዎች እንዲቃወሟቸው የሚያደርጉ የሰይጣን ወኪሎች እነዚሁ ከሃዲያን ናቸው።

> **«በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ»**
> (2ኛ ጢሞ 3፥12)

በዚህ የስደት ጊዜ የጌታ አገልጋዮች እምነት ይፈተናል። እግዚአብሔርንና ቃሉን በመመልከት ብቻ ማስጠንቀቂያውን በታማኝነት አስተላልፈዋል (አሰራጭተዋል)። የእግዚአብሔር መንፈስ ልባቸውን በማነሳሳት እንዲመሰክሩ አደፋፍሮአቸዋል። በተቀደሰ ቅንአት ተነሳስተውና የእግዚአብሔር መንፈስ በሰጣቸው ጠንካራ ኃይል ተደግፈው እግዚአብሔር የሰጣቸውን ቃል ለሕዝብ በመናገራቸው የሚከተለውን መዘዝ ሳያስቡ ግዴታቸውን ተወጡ። እነርሱ ስለ ምድራዊ ጥቅማቸው፤ዝናቸውም ሆነ ሕይወታችን አደጋ ይደርስበታል ብለው አላሰቡም። ይሁንና የተቃውሞና የዘለፋ ማእበል በእነርሱ ላይ በሚነሳበት ጊዜ አንዳንዶቹ ከድንጋጤ የተነሳ «የቃላችን ውጤት ይህ መሆኑን አስቀድመን ብናውቅ ኖሮ ባንናገር ይሻለን ነበር» ብለው ለመናገር የተዘጋጁ ይሆናሉ። እነርሱም በችግር ይከበባሉ። ሰይጣንም በብርቱ ፈተና ያስጨንቃቸዋል። የጀመሩትን ሥራ መፈጸም ከአቅማቸው በላይ የሆነና ለመፈጸም የሚያስቸግርም ይመስላቸዋል። የግድያ ማስጠንቀቂያም ይሰጣቸዋል። ከዚህ በፊት አነሳስቶአቸው የነበረው ጽኑእ የፍላጎት ስሜትም ይርቃቸዋል። ቢሆንም ወደኋላ አይመለሱም። ከዚያም ያለ አንዳች አጋዥ ብቻቸውን መሆናቸው ሲሰማቸው ኃይሉ አምላክ ብርታቱን ይሰጣቸው ዘንድ ወደ እርሱ ይሸሻሉ። የተናገሯቸው ቃላት ሁሉ ማስጠንቀቂያውን እንዲያስተላልፉ ያዘዛቸው የእግዚአብሔር እንጂ የእነርሱ ቃላት አለመሆናቸውን ያስታውሳሉ። እግዚአብሔር በልባቸው እውነትን ዘርቶአልና ይህንን እውነት በግልጽ ከማሰራጨት (ከመናገር) ሊቆጠቡ አልቻሉም።

ባለፉት ዘመናትም ሁሉ ተመሳሳይ ፈተናዎች በእግዚአብሔር ሰዎች ላይ ደርሶባቸው ነበር። ዋይክሊፍ፣ሃስ፣ሉተር፣ቲንደል፣ባክስተር፣ዌይስሊ፤ እነዚህ ሁሉ እያንዳንዱ የሃይማኖት ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ መመዘንና መፈተን እንዳለበት እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ የሚኮንነውን ነገር ሁሉ እንደማያደርጉ አጥብቀው ተናግረዋል (አሳስበዋል)። በእነዚህ ሰዎች ላይ ጭካኔ

*(በገጽ 8 ይቀጥላል)*

## ክፍት የሥራ ቦታ ... ከገጽ 3 የዞረ

አቅጣጫዎች ለጥምቀት የተዘጋጁ ሰዎች ነበሩ። ከዲለላ፣ካመያ አካባቢ የመጡ ነበሩ። ትኩረቴን እጅግ የሳበው ደግሞ ከጉሙዝ ብሄረሰብ 13 ሰዎችን አዘጋጅተው ነበር። ታሪኩ እንዲህ ነው፦ የወሊሶ ቤ/ክን ፈቃደኛ አገልጋይ የሆነው ወንድማችን መሰለ ኪታቦ የጤና ባለሙያ በራሱ መ/ቤት ለሥራ ጉዳይ ወደነዚህ ጉሙዝ ብሄረሰቦች መምሪያ ይላካል። ከወሊሶ በግምት ወደ 40 ኪ/ሜ ያህል ርቀት አለው። እነዚህ ብሄረሰቦች በሚኒሊክ ዘመን ከአሶላ ክልል እንደመጡ ይነገራል፤ህብረተሰቡ ከጉሙዝ ቋንቋ ሌላ ኦሮምኛ መናገር ይችላሉ፤አቶ መሰለ ምንም እንኳን ቋንቋቸውን ባያውቅም እነዚህን ብሄረሰቦች ሲመለከት ያዝናል ምክንያቱም በጣም ኋላ ቀር አኗኗር መኖራቸውን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን የማያውቁ በቃልቻ አምልኮ የተያዙ ጋያ ሜጤስ፣ጫት መቃም፣አረቄ መጠጣት በብሄረሰቡ ዘንዴ እጅግ የተለመደ ነው። ወንድም መሰለ ከዚያ ስፍራ ሲመለስ ራእይ ነበረው «እነዚህ ወገኖች ምነው ጌታን ቢቀበሉ?» አዎን ከመንደሩ ውስጥ አንድ ጥቂት አማርኛ መናገር የሚችሉ አቶ ታደሰ የተባሉ በሥራ አማካይነት ለቀረበው ሰው ስለ መጽሐፍ ቅዱስ በጠቅላላው እምነቱን አካፈለው። «እንግዲህ ይህን ነገር ብቻዬን ሳይሆን በሰፊው ኑና አስተምሩን» በማለት ይለያያሉ በቀጠሮው እለት አቶ መለሰ የወሊሶ ቤ/ክን ወንጌላዊን እንዲሁም ሌሎች ኦሮምኛ ቋንቋ የሚችሉትን ፈቃደኛ አገልጋዬች ይዞ ይሄድና ማስተማር ጀመሩ። ከዚያማ እሳቱ መቀጣጠል ጀመረ። በቀጣይነት አንድ አገልጋይ እዚያ ተቀምጦ እንዲያስተምራቸው መደብን።

በቃልቻ ተይዘው የነበሩ አንድ አሮጊት ሴትዮ ከነልጆቻቸው፣አቶ ታደሰና ቤተሰቡ የመጀመሪያ ፍሬዎች ሆነው 13 ሰዎች በጥምቀት ተቀላቀሉ። የወሊሶ ቤ/ክን ምእመናን የትራንስፖርት እና የቀለብ ሁሉ ወጭያቸውን ሸፍነው ተንከባክበው ለጥምቀት እንዲበቁ አድርገዋል። ክርስትና ማለት ይሄ ነው! እኔ በዚያን እለት ምስክርነታቸውን ስሰማ እንባ ሲተናነቀኝ ነበር። ከምስክርነታቸው በጥቂቱ፦

«እኛ ከሰው ያልተቆጠርነውን የተናቅን ብሄሮች በሰይጣን ታስረን የነበርነውን እግዚአብሔር ከእስራታችን ፈታን አከበረን ከእንደናንተ ወገኖች ጋር እንድንቀላቀል አደረገን ከእንግዲህ በቀረን ዘመን ለክብሩ እንድንቆም ጸልዩልን።» በዚያ ስፍራ ያለው አገልጋይ አሁንም ያንን ያልታረሰ መሬት በወንጌል ማረሻ እያረሰ ነው። ጸልዩለት ጌታ ቢፈቅድ በሌላ ጊዜ ከነዚህ ወገኖች ሌላ ተጠማቂዎች ይኖሩናል። በአካባቢያቸው ቤ/ክን እንሠራላቸዋለን። አቅማችን ቢፈቅድ ክሊኒክ ቢሠራላቸውም ደግሞ ሌላው በጤና በኩል ያላቸውን ትልቅ ችግር ይቀረፋል ብዬ አምናለሁ።

ይህንን ለአብነት ያህል አልኩ እንጂ በየስፍራው ተአምራቶች ይፈጸማሉ። በየጊዜው በስልክ ከየንኡስ ሰበካ ሥራ መሪዎች የምንሰማው ዘገባ አስገራሚ ነው። በቅርቡ ከወሊሶ ክሩሴይድ በኋላ በጅማ ስለተደረገው ታላቅ የወንጌል ጥረት ሳላወሳ ባልፍ ተወቃሽ እሆናለሁ። ከአንድ ወር በፊት ከሰኔ 5 እስከ 15/1996 ለ10 ተከታታይ ቀናት በየምሽቱ በጅማ ሰርከስ አሞራ መሰብሰቢያ ስፍራ ክሩሴይድ አካሂደናል። ስፍራው እስከ 4000 ህዝብ ይይዛል ተብለን ተከራየነው፤ሆኖም ስፍራው በሰው ተጨናንቆ ቦታው ሊይዝ ከሚችለው በላይ ብዙዎች ቆመው መልእክታችንን ይከታተሉ ነበር። ከዋናው የስብከት አገልግሎት በፊት ለ15 ደቂቃ የጤና ትምህርትና የቤተሰብ ትምህርት በባለሙያዎች ይቀርብ ነበር። መልእክቱ በPower Point) የተደገፈ ነበር አቀራረባችንን ህዝቡ በጣም ወዶታል። በመጨረሻም ከ300 ሰዎች በላይ ትምህርታችንን ለመከታተል የውሳኔ ካርድ ሞልተዋል። እነዚህን ሰዎች መከታተል በዚያ ስፍራ ያሉ አገልጋዮችና ምእመናን ሆኖ ሳለ በጣም የገረመኝ የህዝቡ አስተያየት ነው፦ «እናንተ አድቬንቲስቶች ይህንን አይነት የነጠረ እውነት ይዛችሁ ለዘመናት ተኝታችኋል። ከሌሎች ፕሮቴስታንት ቤ/ክች ይልቅ አምልኮአችሁ ስርአት ባለው መልኩ ስለሆነ ወደነዋል» ምእመናኖቻችን ደግሞ አስተያየት ሲሰጡ፦ «ለ40 አመት ተደብቀን ነበር ዛሬ ግን በከተማው በሙሉ ትምህርታችን ተስተጋባ፤ቀና ብለን መሄድ ቻልን» ብለው በእንባ ሲያመሰግኑ ተስተውለዋል። ብዙዎች እባካችሁ ደጋግማችሁ ይህን አይነት ፕሮግራም አካሂዱልን ብለውናል።

## ወንጌል በኢትዮጵያ



በአዲስ አበባ ውስጥ በቁጥር 14 ቤ/ክናት ደርሰዋል። በእርግጥ 5 ያህሉ በኪራይ ቤት፣ሁለቱ ደግሞ ዳስ በመሥራት ጌታን ያመልካሉ።በጣም ደስ የሚለው በየስፍራው ዛሬ ሁሉም የራሱን ማምለኪያ ቤት ለመሥራት ደፋ ቀና ይላል። ምእመኑ የበላይ መሥሪያ ቤትን ደጅ መጥናት ትቶ ወደ ሰማይ አምላክ ይጸልያል፣ ያገኛል፣ ይሠራል።

እንግዲህ ሁሉን ለመዘርዘር ጊዜውም አይበቃኝም። ጥቂት ይህን ያህል ካልኩኝ በማጠቃለያዬ ላይ ለማለት የምወደው ነገር ቢኖር ዛሬ በኢትዬጵያ የሥራ በር ተከፍቷል። ይህ የእግዚአብሔር የሥራ ዘመን ነው።

«መከሩ እጅግ ብዙ ነው ሰራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው» (ማቴ 9፣37) ጌታ «ማንን ልላክ?» ይላል። ኢሳያስ «እኔን ላክ» አለ። ዮናስ ደግሞ «አይ እኔ አልሄድም» ሌላውን ላክ አለ። ጌታ ዛሬ ወደ ነነዌ የሚሄዱትን አገልጋዮች ይፈልጋል። በዚህ በተከፈተው በር የምንሠራበት ጊዜ ቢኖር ዛሬ ነው፤ስለዚህ ሁላችንም በአቅማችን እንሥራ። ስፍራው ድረስ ሄደን ለመሥራት ባንችል እንኳን፤በጸሎት እንዲሁም አቅማችን በሚፈቅደው ሁሉ የሰውን ኃይል ለመደገፍ እንትጋ። ጌታ ጸጋውን ያብዛላችሁ! ◆

*ፓ/ር በቀለ ገብሬ,*
*የመካከለኛ ኢትዮጵያ ሰበካ ፕሬዚደንት*

### ወንድም ዊልያም (ከገጽ1 የዞረ)

«እባክን አትሂድብኝ። አባትህ መርከበኛ ነበር ሕይወቱን ያጣው ባህር ላይ ነው።ወንድምህ ዊልያምም ከአመታት በፊት በባህር ላይ ተጓዘ፤ ስለሱም ሰምተን አናውቅም፣ አሁን ደግሞ አንተ ከሄድክ ትጠፋለህ እኔም ብቻዬን እቀራለሁ» እያለች ተማጸነችው። እሱ ግን «እማዬ ይህንን ሰው ማዳን አለብኝ» ብሎ ስሚት ተሰናበታት። ጎልማሳውና ፈቃደኛው ሰው በዚያ ጥቅጥቅ ባለ ጨለማና ጉም ውስጥ ያንን ምስኪን ወጣት ለማዳን ወደ ተሰበረችዋ መርከብ በጀልባ መቅዘፍ ጀመሩ። በባህር ዳር ላይ የነበሩት ሰዎችም ለረዥም ጊዜ የነሱን መመለስ ሲጠባበቁ ከርቀት በድንግዝግዝ አንዲት ጀልባ ወደነሱ ስትቀዝፍ አስተዋሉ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጀልባዋ ቀረብ ስትል በባህር ዳር ላይ ካሉት ሰዎች አንዱ ጀልባዋ ላይ ወዳለው ጎልማሳ በመጣራት «ያንን ምስኪን አዳንከውን?» ሲል ጠየቀው። ጎልማሳውም «አዎን አግኝቼዋለሁ ለናቴም ወንድሜን ዊልያምን እንዳገኘሁ ንገራት» አለው። ይህ ጎልማሳ ተጓዘና ወንድሙን አገኘው። ይህም የእኔና የናንተ ሥራ ነው። ብዙ «ወንድም ዊልያሞች» በተሰበረችው መርከብ ላይ አሉና። እነዚህንም አምጥተን ለሰማይ እረፍት ማድረስ እንድንችል እግዚአብሔር ይርዳን። ◆

*ጆርጅ ቢ. ቶምሰን*

***Sign of the times June 19, 1917***

አ
ዲ
ስ

መ
ጽ
ሐ
ፍ




አዲስ እጅግ ጠቃሚ የሆነ የጤና መጽሐፍ በኢትዮጵያ አድቬንቲስት ማተሚያ ቤት ታትሞ ለሽያጭ ቀርቦአል። ለበለጠ መረጃ በአ.አ. የአድቬንቲስት መጽሐፍት መደብር ይጠይቁ።

# የትንቢት ቃል

Yetnbit Kal
P.O.Box 1749
90006 Nuernberg
Germany

Editors:
Dawit Mehari
Dawit Mengistu

Tel & Fax 0049 - 911- 41 57 89
Tel & Fax 0049 - 89 - 22 24 48
E-Mail: dawit.mehari@mail.com
E-Mail: dawitmengistu@web.de

ይህንን የጽሑፍ አገልግሎት በገንዘብ ለመደገፍ የምታስቡ ሁሉ በዚህ የባንክ ቁጥር መጠቀም ትችላላችሁ። ለድጋፋችሁ በቅድሚያ ከልብ እናመሰግናለን እግዚአብሔር ይባርካችሁ!
Sparkasse Nürnberg,
Yetnbit Kal,
Account Nr.: 2 059 932
BLZ: 760 501 01

ይህች «የትንቢት ቃል» የምትለው የአድቬንቲስት መጽሔት በጀርመን አገር ተዘጋጅታ በየሶስት ወር ትወጣለች። አላማዋም በአገራችንና በተለያዩ አህጉራት የሚገኙትን ወገኖቻችንን ለየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ለማዘጋጀት ነው። ምንም ዋጋ የማይከፈልባት በነጻ የምትላክ እንደሆነች ልንገልጽልዎ እንወዳለን። ስለዚህ ለእርስዎም ሆነ ለሌሎች ጽሑፉ እንዲደርሳቸው ለሚፈልጉት ሰዎች አድራሻዎችን ቢያሳውቁን መጽሔቱን እንልካለን።

በዚህች መጽሔት መልእክት ተባርከው እንደሆነና አስተያየትም ሆነ ጥያቄ ካለዎ ሃሳብዎን ቢገልጹልን በጣም ደስ ይለናል።

*የመጨረሻው ... (ከገጽ 6 የዞረ)*

የተሞላበት ስደት ደርሶባቸዋል። ሆኖም እነርሱ እውነትን ከመናገር አላረፉም። በቤተክርስቲያን ታሪክ የተለያዩ ክፍለ ጊዜያት ወቅት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ልዩ እውነቶች ጎልተው በገሃድ ይገለጡ ነበር። እነዚህም እውነቶች በዛን ጊዜ ለነበሩ የእግዚአብሔር ሰዎች ጠቃሚ የነበሩ ናቸው። በዘመኑም ይገለጥ የነበረው እያንዳንዱ አዲስ የእውነት ብርሃን በጥላቻና በቅራኔ መንገድ ነበር ያለፈው። በዚህ አዲስ የእውነት ብርሃን የተባረኩ ሁሉ ፈተና ገጥሞ አቸዋል።

አስፈላጊ በሆነበት ወቅት ጌታ ለሕዝቡ ከቃሉ ልዩ እውነትን ይገልጣል። ማነው ደፍሮ ይህንን እውነት አላውጅም የሚል? ለአለም የመጨረሻውን የምሕረት ግብዣ እንዲያስራጩ እግዚአብሔር አገልጋዮችን ያዛል። አገልጋዮቹም ከዚህ አለም በሞት እስካልተለዩ ድረስ በዝምታ ለመቆየት አይችሉም። የክርስቶስ አምባሳደሮች ሁኔታው ስለሚያስከትለው ውጤት ምንም አያገባቸውም። እነርሱ ግዴታቸውን መፈጸምና ውጤቱን ለእግዚአብሔር መተው ብቻ ነው ያለባቸው። ◆ <u>*ይቀጥላል*</u>

*ኤለን ጂ. ዋይት*

## የጥያቄዎ መልስ

### መጽሐፍ ቅዱስ እንድናከብራቸው የሚመክረን በአላት የትኞቹ ናቸው?

<u>*አቶ ዳ.መ. ከጀርመን*</u>

ይህንን ጥያቄ ከመመለሳችን በፊት«እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ዘመን ለእስራኤል ሕዝቦች እንዲያከብሩ ያዘዛቸው በአላት የትኞቹ ነበሩ?» ለሚለው ጥያቄ መልስ እንስጥ። በብሉይ ኪዳን ጊዜ በሳምንት አንዴ እንዲሁም በየአመቱ እንዲከበሩ የታወጁ በአላት የሚከተሉት ናቸው፦

1) ሰንበት። «...የተቀደሰ ጉባኤ ብላችሁ የምታውጁአቸው በአላቶቼ የእግዚአብሔር አባላት እነዚህ ናቸው፦ ስድስት ቀን ሥራ ይሠራል በሰባተኛው ቀን ግን የእረፍት ሰንበት ነው፤የተቀደሰ ጉባኤ ይሆንበታል፤ምንም ሥራ አትሠሩም በምትኖሩበት ሁሉ ለእግዚአብሔር ሰንበት ነው» (ዘሌ 23፥2-3 ፤ ዘጸ 20፥8-11)

2) ፋሲካ ወይም የቂጣ በአል (ዘሌ 23፥5-8)። ይህ የእስራኤል ከግብጽ አገር ከባርነት የመውጣታቸው መታሰቢያ በአል ነው። ፋሲካ በእብራይስጥኛ «ፓሳህ» ሲባል ትርጉሙም «አለፈ» ማለት ነው።

3) የመከር በአል (ዘጸ 23፥16)። ይህ በአል ሰባት ሳምንት ከፋሲካ በኋላ ይከበራል (ዘዳ 16፥9-12) የስንዴ አጨዳ ሲጀመር የመከር በአል (ሰባቱ ሱባኤ) ይከበራል። በአሉ የምስጋናና የደስታ ጊዜ ነው።

4) የዳስ በአል (ዘዳ 16፥13 ፤ ዘሌ 23፥39-43) ወይም የአዝመራ ማከማቻ በአል በመባል የሚታወቀው በአል በ7ኛው ወር በ15ኛው ቀን እህል ከተከማቸ በኋላ የእስራኤል ልጆች ሰባት ቀን በዳስ ውስጥ ተቀምጠው የበረሃ ሕይወታቸውን የሚያስታውሱበትና አምላካቸውን የሚያመሰግኑበት በአል ነበር።

5) የመቅደስ መታደስ መታሰቢያ በአል። በ9ኛው ወር በ25ኛው ቀን ሶሪያውያን ቤተ መቅደሱን ካረከሱት በኋላ እንደገና የተመረቀበትን/የታደሰበትን ቀን ለማስታወስ የታወጀ በአል ነበር። ዮሐ 10፥22

6) መለከት የሚነፋበት ቀን በ7ኛው ወር በ1ኛው ቀን ይከበር ነበር። (ዘሌ፥23-24፤ዘኁ 29፥1)

7) የማስተሰሪያ ቀን በ7ኛው ወር በ10ኛው ቀን አይሁድ ሁሉ ራሳቸውን እያዋረዱ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ይለምኑ ነበር (ዘሌ 23፥26-32)። በዚያን ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ ሥራቸውን ሁሉ ትተው ይጾሙ ነበር። በዚህ ቀን ኃጢያታቸውን ይናዘዛሉ። ሊቀ ካህናቱም የማእረጉን ልብስ አውልቆ ሌላ ልብስ በመልበስ መጀመሪያ ለራሱና ለቤተሰቡ፤ቀጥሎም ለሕዝቡ መስዋእት ያቀርባል። በየአመቱ በዚህ ቀን ብቻ ደሙን ይዞ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ይገባል። ከዚያም በታቦቱ መክደኛ ላይ ደሙን ይረጫል። በዚያን ቀን ሃጢያቱን ሳይናዘዝ የተገኘ ቢኖር እርሱ ሞት ይፈረድበታል።

8) ፉሪም። በአስቴር ዘመን አይሁድ ከጠላቶቻቸው እረፍትን ያገኙባቸው ቀኖች ሲሆኑ በ12ኛው ወር በ14ኛውና በ15ኛው ቀን የደስታ በአል እንዲደረግባቸው ታውጆአል (አስ 9፥16-28)።

እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው በአላት እስከ የሱስ ስቅለት ድረስ ሲከበሩ እንደቆዩ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። በሃዋሪያት ዘመንም ሆነ ከዚያ በኋላ የክርስትና ሃይማኖት በተስፋፋበት ዘመናት ሁሉም በአላት ሲከበሩ ግን አይታዩም። በአዲስ ኪዳን ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱትና የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ዘወትር ያከብሩአቸው የነበሩት በአላት የሰባተኛው ቀን ሰንበት (ሐዋ 16፥13፤ ሐዋ 13፥42+44) እና የጌታ እራት (ሉቃ 22፥14-20 ፤ 1ኛ ቆሮ 11፥23-26 ፤ ዮሀ 13፥1-17) ነበሩ።

ከ300ኛው ዓ.ም. ጀምሮ በወቅቱ የነበረችው ቤ/ክ የቀድሞ እስራኤል ሕዝብ አንዳንድ ያከብራቸው የነበሩትንና ሌሎች አዳዲስ በአላትን ጨምሮ (ፋሲካ፤ገና/ልደት፤ጴንጤቆስጤ፤ መስቀል፤ አዲስ አመት፤የመከር ምስጋና በአል...) እንዲሁም አንዳንድ የአሕዛብ በአላትን የክርስትና ካባ በማልበስና ከክርስትና ሃይማኖት ትምህርት ጋር በማዛመድ አስገብታለች።

በእርግጥ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን መወለድ፤የምድር ሕይወቱንና ሞቱን የሚያስታውሱንን ልዩ ጊዜዎችና አጋጣሚዎች ማግኘት መልካም ነው። ይህንን ለማድረግ የተለዩ ቀናትን መወሰን ባንገደድም፤ዘወትርም ሆነ ባገኘናቸው አጋጣሚዎች እነዚህን ማሰብና ማስታወስ እንዲሁም ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ንጹሁን ወንጌል ላልሰሙት ማሳወቅ ተገቢ ነው። ቢሆንም እግዚአብሔር በሚፈልገውና ባዘዘው መንገድ ሳይሆን እኛ በምንፈልገውና በሚመቸን ሰው ሰራሽ ወግና ስርአት እንዲሁም ከባእድ አምልኮ ጋር የተያያዙ በአላትን ማክበር በክርስቶስ እንደገና ለተወለዱ አዲስ ፍጥረቶች ተገቢ አይደለም። በመሆኑም ሁሉን በመፈተንና መልካሙን ብቻ በመያዝ ከማናቸውም አይነት ክፉ ነገር መራቅ የክርስቲያን ግዴታ ነው (1ኛ ተሰ 5፥21-22)። ◆